

# ወደ ኡመዮ — የ2014 ዓ.ም የኤውሮጳ የባህል መዲና- እንኳን በደህና መጡ

**የኡመዮ ከተማ: በ "Future Flows Through Us" የሚታወቀውን ምረቃ በመጠቀም በተቀረው የባህል መዲና የዐመት ወቅት የሚጠበቁትን ጉዳዮች ቅርጽ ታስይዛለች። በፌስቲቫል: በስነ-ጥበብ መድርክ: በኦፐራ: በስነ-ጽሁፍ: በፊልም: በሙዚቃ: በስነ-ጥበብ: በዕደ-ጥበብ: በስፖርትና በሌላ መልክ የሚቀርቡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ፍጻሜዎች።**

የኤውሮጳ ህብረት ምክር ቤት ኡመዮ የ2014 ዓ.ም. የባህል መዲና እንድትሆን ሰይሞአታል። የኤውሮጳ ህብረት የባህል መዲኖችን የመሰየም ዐላማ: የባህል ብዙነት ለማንጸባረቅ: የባህል ልውውጥ ከፍ ለማድረግና በኤውሮጳ የባህል ቅርስ ንቃት ለማስነሳት ነው። የመጀመሪያዋ የባህል መዲና ብ1985 የተሰየመችው ግርክ አገር የምትገኘው የአቴንስ ከተማ። በአሁኑ ጊዜ ባመት ሁለት ከተሞች ነው የሚሰየሙት፤ በዚህ ምክንያት በላትቭያ የምትገኘው የሪጋ ከተማም በተመሳሳይ ለ2014 ዓ.ም. ተሰይማለች።

የኡመዮ ከተማና ሰሜናዊው የስዊድን ክልል በኤውሮጳ እውቅ ለማድረግ: ክልሉን ለማልማት ባህልን እንደ ገፊ ኃይል የመጠቀም ያለው ፍላጎት ምስጋና ይግባውና ኡመዮ የባህል መዲና ለመሆን በቅታለች። የሚደረገው ዋና ትኩረት በኡመዮ ከተማ ይሁን እንጂ ሌሎች በክልሉ ያሉት ቦታዎችም ሚና ይጫወታሉ።

## የብዮርክ ዛፍ ከተማ

ኡመዮ በሰሜን ስዊድን በቬስተርቦተን ክልል ትገኛለች፤ 118 000 ኗሪዎችም አሏት። ከተማዋ ብዙ የውጭ መዝናኛ ቦታዎች አሏት። የከተማዋ የተፈጥሮ ቦታዎችም ሁልጊዜም ቅርብ ናቸው። በኡመዮ ከተማ አካባቢ: የባህር ዳር: ሐይቆች: ጫካዎችና የአካል እንቅስቃሴ የሚደረግባቸው ቦታዎች አሉ። የወርጭ ጉዞ የሚደረግባቸው መደዳዎችና ኮረብታች አሉ። የኡመዮ ከተማ ኗሪዎች ብስኪሌት ይነዳሉ፤ ምክንያቱም ያለው የቦታዎች ርቀት እስከዚህም ነው፤ የትም ቦታም የቢስክሌት መንገዶች አሉ።

በ1888 ዓ.ም. የተነሳው የእሳት ቃጠሎ ከተማዋን በከፊል አውድሞአል። ከተማዋ እንደገና ስትቆረቆር እሳት ገብቶ እንዳያበላሽ ለመከላከል በመንገዶች ዳር የብዮርክ ዛፎች ተተከሉ። በዚህ ምክንያት ነው ደግሞ ኡመዮ በዘልማድ "የብዮርክ ዛፍ ከተማ" ተብላ የምትጠራው።

## ሃብታም የባህል ህይወት

ኡመዮ ዩኒቨርስቲ: ተማሪዎች: አስተማሪዎችና ተመራማሪዎች የሚገኙበት ከትላልቅ የስዊድን ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ነው።

እነዚህ ተማሪዎች ከብዛታቸው የተነሳ የኡመዮ አማካይ ዕድሜ ታች እንዲወርድ አድርገዋል። በኡመኤልቨን ጅረት አከባቢ በዲዛይን: በስነ-ጥበብና በስነ-ህንጻ የላቀ ትምህርት የሚሠጠው "ኮንስትነርሊት ካምፑስ" የተባለው ካምፑስ አለ። እዛው ቦታ በዘመናዊ ስነ-ጥበብ ዕውቅ ቦታ የሚይዘው "ቢልድሙሲየት" የተባለውም አለ።

ኡመዮ: ትያትር ቤቶች: ቤተ-መዘክሮችና የሙዚቃ መድረኮች ያጠቃለለ ሃብታም የባህል ህይወት አላት። "ኖርላንድ ኦፐራ"ን እንደ ምሣሌ መጥቀስ ይቻላል፣ በያመቱ ብዙ ኢንተርናሽናል የባህል ፌስቲቫሎች ይዘጋጃሉ፤ አብዛኞቹ የባህል ማኅበሮችም በንቃት ይሳተፋሉ። ብዙ የሙዚቃ ባንዶች አሉ፤ አብዛኞቹም ኢንተርናሽናል ዝና ያተረፉ ናቸው።

## ትብብራዊ ፈጠራ

የኡመዮ የባህል መዲና ያመት መደብ: በሳመ ብሔሰብ የዐመት አቆጣጠር መሠረት: በስምንት የተከፈለ ነው። ሳሞች የኤውሮጳ ህብረት የብቻ ብሔረሰብ ተወላጆች ናቸው፤ ኡመዮም በምድረ-ሳመ (ሳፐሚ) ትገኛለች።

ትብብራዊ ፈጠራ በኡመዮ የባህል መዲና ጥረቶች ታላቅ ሚና ይጫወታል። ሁሉ ፍላጎት ያለው ግለሰው ባመቱ መደቦች መሳተፍና ላመቱ መደቦች አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላል። ብ2014 ዓ.ም. የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በማኅበሮች: በድርጅቶች: በባህል ኢንስቲቱሽኖችና በሌሎች ከ"ኡመዮ2014" ድጋፍ የሚያገኙ ተካፋዮች ይዘጋጃሉ። እነዚህ: ባመቱ የባህል መዲና የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ከ2014 ዓ.ም. በሁዋላም ቀጣይነት እንደሚኖራቸው ያረጋግጣሉ።

የባህል መዲና ዘመቻው: የግኑኝነት ቦታዎች: የኔትወርክ: የኢንተርናሽናል ትብብሮችና ዕድሎች ለምፍጠር ዐላማ ያለው ከከተማችን የረጂም ጊዜ የልማት መደቦች — ማለትም በባህልና በማኅበራዊ መስኮች ጭምር - አንዱ ክፍል ነው።

በድኅረ-ገጽ አድራሻው www.umea2014.se ያመቱ የባህል መዲና መደቦች በስዊድንኛና በእንግሊዝኛ ተዘጋጅተው ቀርበዋል።

UMEÅ2014 EUROPEAN CAPITAL OF CULTURE

EUROPEAN CAPITAL OF CULTURE